# መጽሀፍ ቅዱስ የሚነሱ ጥያቄዎችን እንዴት እንመልስ?

# የመለኮታዊ መጽሐፍ ቁርአናዊ መለኪያዎች፡-

ከአላህ ዘንድ የወረደ መሆን ይኖርበታል

ሱረቱል አሽ-ሹራ 26 ፡ 192-193

እርሱም (ቁርኣን) በእርግጥ ከዓለማት ጌታ የተወረደ ነው፡፡ እርሱን ታማኙ መንፈስ (ጂብሪል) አወረደው፤

እውነተኛ /እውነት/ መሆኑ

ሱረቱል አር-ረድ 13 ፡ 1

...ይህች (አናቅጽ) ከመጽሐፉ አንቀጾች ናት፡፡ ያም ከጌታህ ወዳንተ የተወረደው እውነት ነው፡፡ ግን አብዛኞዎቹ ሰዎች አያምኑም፡፡

# የቀጠለ

## በአላህ ጥበቃ ውስጥ የኖረ እና ለትውልድ ያለምንም እንከን መተላለፍ የቻለ

**ሱረቱል አል-ሒጅር 15 ፡ 9**

እኛ ቁርኣንን እኛው አወረድነው:: እኛም **ለእርሱ ጠባቂዎቹ** ነን::

## እርስ በእርሱ የማይጣረስ

**ሱረቱል አል-ኒሳእ 4 ፡ 82**

ቁርኣንን አያስተነትኑምን? ከአላህ ሌላ ዘንድ በነበረ ኖሮ በርሱ ውስጥ ብዙን **መለያየት ባገኙ** ነበር::

## ከሰው እና ከሰይጣን ጣልቃ ገብነት ነጻ የሆነ

## ሱረቱል አል-በቀራ 2 ፡ 23

**በባሪያችንም ላይ ካወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ብትኾኑ** ከብጤው አንዲትን ምዕራፍ አምጡ:: እውነተኞችም እንደኾናችሁ ከአላህ ሌላ መስካሪዎቻችሁን ጥሩ::

# በመጽሀፍ ቅዱስ ላይ ጥያቄዎች ሲነሱ መመለስ ያልብን እንዴት ነው?

1. ጥያቄው የተጠየቀበትን መሰረት/ ምንጩን መረዳት
2. ጥያቄውን በጥያቄ መመለስ
3. የሚጠየቁ ጥያቄውች ፍርደ ግምድልነት ካለባቸው በጥንቃቄ መመርመር

# መጽሀፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ያልሆነበት ምክንያት

# የጳውሎስ የግል መልእክት በአምላክ ቃል ውስጥ መካተቱ

2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 4 ፡ 9-13

በቶሎ ወደ እኔ እንድትመጣ ትጋ፤ ዴማስ የአሁኑን ዓለም ወዶ ትቶኛልና፥ ወደ ተሰሎንቄም ሄዶአል፤ ቄርቂስም ወደ ገላትያ ቲቶም ወደ ድልማጥያ ሄደዋል፤ ሉቃስ ብቻ ከእኔ ጋር አለ። ማርቆስ ለአገልግሎት ብዙ ይጠቅመኛልና ይዘኸው ከአንተ ጋር አምጣው። ቲኪቆስን ግን ወደ ኤፌሶን ላክሁት። ስትመጣ በጢሮአዳ ከአክርጳ ዘንድ የተውሁትን በርኖሱንና መጻሕፍቱን ይልቁንም በብራና የተጻፉትን አምጣልኝ።

አብዛኛው የሙስሊም ምሁራን ጳውሎስ በርኖሱንስ እና መጻሕፍቱን አምጣልኝ ብሎ የግል ፍላጎቱን መጠየቁ መጽሐፍ ቅዱስን የእግዚብሔር ቃል አያሰኘውም ይላሉ

# የጥያቄው ምላሽ፡

ጥያቄውን ለመለለስ፡ እንዴት በሚለው የአመላለስ ስልት ውስጥ ማሳለፍ እና ጥያቄውን መረዳት

1. ጥያቄው የተጠየቀበትን መሰረት/ ምንጩን መረዳት
   - የአምላክ ቃል የራሱ የአምላክ መሆን አለበት
   - የአምላክ ቃል ከሰማይ የወረድ መሆን አለበት
   - የአምላክ ቃል ውስጥ የሰው ንግግር መግባት የለበትም
2. ጥያቄውን በጥያቄ መመለስ/ ጥያቄውን ገልብጦ መጠየቅ
   - ከአላህ ቃል ውጪ በቁራን ውስጥ የሰፈረ ቃል ካለ ማወቅ ይሄ ጥያቄን በጥያቄ ለመጠየቅ ይረዳናል
3. ጥያቄው ፍርደ ግምድልነት አለበት?
   - የጳውሎስ ፍላጎት ማለትም በርኖሱን እና መጽሐፍቱን አምጣልኝ ያለው ቃል መጽሀፍ ቅዱስን የአምላክ ቃል አይደለም ካሰኘ ከአምላክ ቃል ወጪ ቁራን ውስጥም ቢገኝ ቁራንን የአምላክ ቃል እንደማያሰኘው መረዳት

# በቁራን ውስጥ ከአላህ ቃል ውጪ መኖሩ

ሱረቱል አል-ጂን (የጋኔን ምዕራፍ) 72 ፡ 1-4

(ሙሐመድ ሆይ!) በል «እነሆ ከጂን የኾኑ ጭፍሮች (ቁርኣንን) አዳመጡ፡፡‹እኛ አስደናቂ የኾነን ቁርኣን ሰማንም› አሉ፣ ማለት ወደእኔ ተወረደ፡፡ ‹ወደ ቀጥታ መንገድ የሚመራን (ቁርአን ሰማን)፡፡ በእርሱም አመንን፡፡ በጌታችንም አንድንም አናጋራም፡፡› ‹እነሆም የጌታችን ክብር ላቀ፡፡ ሚስትንም ልጅንም አልያዘም፡፡› ‹እነሆም ቂላችን በአላህ ላይ ወሰን ያለፈን (ውሸት) ይናገር ነበር፡፡›

# ማን ነገራቸው

ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 5፣ ቁጥር 3859

ጅኖቹ በምሽት ቁርአን ሲቀራ ማድመጣቸውን ለነቢዩ ማን ነገራቸው? ስል ማስሩቅን ጠየቅኩት፤ እርሱም ጅኖቹ ቁርአኑን በምሽት ማድመጣቸውን፣ ለነቢዩ የነገራቸው ዛፍ ነው ሲል አባትህ አብዱላህ ነግሮኛል፤ አለኝ፡፡ አብዱር-ራህማን የተናገረው ሐዲስ ነው172

# መደምደሚያው

መጽሀፍ ቅዱስ የእግዚያብሄር ቃል ነው ስንል

- የእግዚያብሄር የራሱ ቃል ብቻ ነው ብለን አናምንም
- መጽሀፍ ቅዱስ ከሰማይ ለሰዎች ተሰጠ ብለንም አናምን
  - መጽሀፍ ቅዱስ ሁለት ጽሀፊዎች እንዳሉት እናምናለን
    - የእግዚአብሔር መንፈስ እና
    - በእግዚአብሔር መንፈስ ተነድቶ የሚጽፈው ሰው
- በዚህም መሰረት ጳውሎስ በርኖሱን እና መጽሀፍቱን አምጣልኝ ማለቱ የአምላክነት ቃሉ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ የለም
- በቁራናዊ መለኪያ ግን የዛፍ ቃል በቁራን ውስጥ መኖሩ የቁራንን የመለኮት ቃልነት ውድቅ እንዲሆን ያደርገዋል

# የጾታዊ የፍቅር ንግግር በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ መገኘቱ

መኃልየ መኃልይ 7 ፡ 1-9 ሀ

አንቺ ሱላማጢስ ሆይ፥ ተመለሽ፥ ተመለሽ እናይሽ ዘንድ ተመለሽ፥ ተመለሽ። በሱላማጢስ ምን ታያላችሁ? እርስዋ እንደ መሃናይም ዘፈን ናት። አንቺ የመኰንን ልጅ ሆይ፥ እግሮችሽ በጫማ ውስጥ እንዴት ውቦች ናቸው! ዳሌዎችሽስ በአንጥረኛ እጅ እንደ ተሠሩ እንደ ዕንቍዎች ይመስላሉ። እንብርትሽ የወይን ጠጅ እንደማይጐድልበት እንደ ተነጠጠ ጽዋ ነው፤ ሆድሽ እንደ ስንዴ ክምር፥ በአበባም እንደ ታጠረ ነው። ሁለቱ ጡቶችሽ እንደ ሁለቱ መንታ እንደ ሚዳቋ ግልገሎች ናቸው። አንገትሽ እንደ ዝሆን ጥርስ ግንብ ነው፤ ዓይኖችሽ በሐሴቦን ውስጥ በባትረቢ በር አጠገብ እንደ ውኃ ኵሬዎች ናቸው፤ አፍንጫሽ ወደ ደማስቆ አፋዛዥ እንደሚመለከት እንደ ሊባኖስ ግንብ ነው።...

# የጥያቄው ምላሽ፡

ጥያቄውን ለመለለስ፡ እንዴት በሚለው የአመላለስ ስልት ውስጥ ማሳለፍ እና ጥያቄውን መረዳት

1. ጥያቄው የተጠየቀበትን መሰረት/ ምንጩን መረዳት
   - የአምላክ ቃል የራሱ የአምላክ መሆን አለበት
   - የአምላክ ቃል ከሰማይ የወረድ መሆን አለበት
   - የአምላክ ቃል ውስጥ የሰው ንግግር መግባት የለበትም
   - የዚህ ጥያቄ ዋና ሀሳብ የኢ_ሞራላዊነት ኢስነምግባራዊነት መሆኑን መረዳት እጅግ አስፈላጊ ነው
2. ጥያቄውን በጥያቄ መመለስ/ ጥያቄውን ገልብጦ መጠየቅ
   - የኢ_ሞራላዊነት እና ኢስነምግባራዊነት የሚስተዋልባቸውን የቁራን ክርሎች ያሉ እንደሆነ ማየት
3. ጥያቄው ፍርደ ግምድልነት አለበት?
   - የመህልዬ መጽሀፍ የኢ_ሞራላዊነት እና ኢስነምግባራዊነት ስላለበት የአምላክ ቃል አይደለም ካስባለው ማንኛውም የሞራል ግድፈት ያለበት የቁራን ክፍል መጽሀፉን ከአምላክ ቃልነት እንደሚያወርደው መገንዘብ

# በመጀመሪያ የክፍሉን ትርጓሜ መረዳት

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ያለውን ኪዳን በጋብቻ በመመሰል ማቅረብ የተለመደ ነው፡፡ እናም አይሁዳውያን እግዚአብሔር አምላክ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ያደረገውን ኪዳን ተምሳሌታዊ በሆነ መልኩ የገለጸበት ቅዱስ መዝሙር እንደሆነ ያምናሉ፡፡ ስለዚህ ይህ ዝማሬ በየዓመቱ ከግብጽ የወጡበትን መታሰቢያ የፋሲካን በዓል ሲያከብሩ በምእራፍ ከፋፍለው ለአንድ ሳምንት ያህል ይዘምሩት እንደ ነበር ትውፊቶች ያስረዳሉ፡፡ እንዲያውም ዝማሬው ቅዱስ ዝማሬ በመሆኑ የዝማሬውን ክብርና ቅድስና እንዳያጎድፉና እንዳያዋርዱ ወጣቶች እድሜያቸው ዝማሬውን ለመረዳት እስከሚደርስ ድረስ እንዳያነቡት ይከለከል ነበር፡፡ ስለዚህ የመኃልየ መኃልይ መጽሐፍ የእስራኤል ሕዝብ እና የእግዚአብሔር የኪዳን ተምሳሌታዊ መግለጫ ዝማሬ እንጂ እንዳሉት የዝሙት መጽሐፍ አይደለም፡፡

ከዚያም የቀጠለው የክርስትናው ዘመን አሁንም ክርስቶስ ለቤተክርስያን እንዲሁም ክርስቶስ ለአንድ ክርስቲያን ያለውን ፍቅር ተምሳሌታዊ በሆነ መልኩ የሚገልጽ መጽሐፍ እንደሆነ ይታመናል ነውም፡፡ በአዲስ ኪዳን መጽሐፍት የጌታችንና የመድሐኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እና የቤተ ክርስቲያን ግንኙነት አሁንም በአህዳዊ ጋብቻ ተመስሎ ተገልጾ እንመለከታለን፡፡

# በመቀጠል በሚዛን ላይ ቁራንን ማስቀመጥ

**ሱረቱል አን-ናባ 78 ፡ 31-33**

ለጥንቁቆቹ መዳኛ ስፍራ አልላቸው፡፡ አትክልቶችና ወይኖችም፡፡ እኩያዎች የኾኑ **ጡተ ጉቻማዎችም**፡፡

**ሱረቱል አል-ሙምታሃና 55 ፡ 70-72**

በውስጣቸው ጠባየ መልካሞች መልከ ውቦች (ሴቶች) አልሉ፡፡ ከጌታችሁም ጸጋዎች በየትኛው ታስተባብላላችሁ? በድንኳኖች ውስጥ የተጨጎሉ የዓይኖቻቸው ጥቁረትና ንጣት ደማቅ የኾኑ ናቸው፡፡

**ሱረቱል አጥ-ጡር 52 ፡ 20**

በተደረደሩ አልጋዎች ላይ ተደጋፊዎች ኾነው (በገነት ይኖራሉ)፡፡ ዓይናማዎች በኾኑ ነጫጭ ሴቶችም እናጠናዳቸዋለን፡፡

# የቀጠለ

ሱረቱል አል-ኒሳእ 4 ፡ 24

ከሴቶችም (በባል) ጥብቆቹ እጆቻችሁ (በምርኮ) የያዙዋቸው ሲቀሩ በእናንተ ላይ እርም ናቸው፡፡ (ይህን) አላህ በናንተ ላይ ጻፈ፡፡ ከዚሃችሁም (ከተከለከሉት) ወዲያ ጥብቆች ኾናችሁ ዝሙተኞች ሳትኾኑ በገንዘቦቻችሁ ልትፈልጉ ለእናንተ ተፈቀደ፡፡ ከእነሱም በርሱ (በመገናኘት) የተጠቀማችሁባቸውን ሴቶች መህሮቻቸውን ግዴታ ሲኾን ስጧቸው፡፡ ከመወሰንም በኋላ በተዋደዳችሁበት ነገር በእናንተ ላይ ኀጢአት የለም፡፡ አላህ ዐዋቂ ጥበበኛ ነውና፡፡

ቁራን ባል ከሚስቱ ውጪ በገንዘቡ ወሲባዊ እርካታን እንዲያገኝ ፈቅዶ ሳለ የመህልዬ መጽሀፍ ዝሙትን ያበረታታል ቢባል ፍርደ ገምድልነት አይሆንም?

የሚቀጥሉትን ክፍሎች ከላይ በተመለከትነው መሰረት እንመልከታቸው

# መጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ የሚታዩ የቁጥር ልዩነቶች

# የአህያዋ መናግር

2ኛ የጴጥሮስ መልእክት 2 ፡ 16

ነገር ግን ስለ መተላለፉ ተዘለፈ፤ ቃል የሌለው አህያ በሰው ቃል ተናግሮ የነቢዩን እብድነት አገደ።

# የቴምር ዛፍ ማለቀስ

ቡኻሪ 2 496፣ ናሳኢና ትርሚዝ የዘገቡት ሐዲስ፡፡"

የአላህ መልዕክተኛ የጁምአ ሁጥባ የሚያደርጉት የቴምር ግንድን በመደገፍ ነበር፡፡ መንበር ከተሠራላቸው በኋላ ግን ያንን የቴምር ግንድ ትተው ወደ ተሠራላቸው መንበር ሲወጡ የቴምር ግንዱ እንደ ግመል መንሰቅሰቅ ተንሰቅስቆ አለቀሰ፡፡ የአላህ መልእክተኛም ወደ እርሱ በመምጣት እጃቸውን ሲያሳርፉበት ወዲያው ጸጥ አለ፡፡

# የረሀቡ ጊዜ ስንት አመት ነው?

**2ሳሙ 24፥13**

ጋድም ወደ ዳዊት መጥቶ። የሦስት ዓመት ራብ በአገርህ ላይ ይምጣብህን? ወይስ ጠላቶችህ እያሳደዱህ ሦስት ወር ከእነርሱ ትሸሽን? ወይስ የሦስት ቀን ቸነፈር በአገርህ ላይ ይሁን? አሁንም ለላከኝ ምን መልስ እንደምሰጥ አስብና መርምር ብሎ ነገረው።

**መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ 21:12**

¹²የሦስት ዓመት ራብ፥ ወይም ሦስት ወር የጠላቶችህ ሰይፍ እንዲያገኝህ ከጠላቶችህ መሰደድን፥ ወይም ሦስት ቀን የእግዚአብሔር ሰይፍ ቸነፈርም በምድር ላይ መሆንን፥ የእግዚአብሔርም መልአክ በእስራኤል ምድር ሁሉ ማጥፋትን ምረጥ፤ አሁንም ለላከኝ ምን እንድመልስ ተመልከት አለው።
¹³፤ ዳዊትም ጋድን። እጅግ ተጨንቄአለሁ፤ ምሕረቱ ብዙ ነውና በእግዚአብሔር እጅ ልውደቅ፤ በሰው እጅ ግን አልውደቅ አለው።

# ሰሎሞን ስንት ጋጣ ነበረው

**መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ 9 13**

ሰሎሞንም ለፈረሶችና ለሰረገሎች አራት ሺህ ጋጥ፥ አሥራ ሁለት ሺህም ፈረሰኞች ነበሩት፥ በሰረገሎችም ከተሞች፥ ከንጉሡም ጋር በኢየሩሳሌም አኖራቸው

**መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ። 2 26**

ለሰሎሞንም በአርባ ሺህ ጋጥ የሚገቡ የሰረገላ ፈረሶች አሥራ ሁለትም ሺህ ፈረሰኞች ነበሩት።

# የቁጥር ልዩነቶች በቁራን

ሰማይና ምድር በስንት ቀኖች ውስጥ ተፈጠሩ?

ሱራ 50: 38

ሰማያትንና ምድርን በመካከላቸው ያለውንም ሁሉ በስድስት ቀናት ውስጥ በእርግጥ ፈጠርን፡፡ ድካምም ምንም አልነካንም፡፡

ሱራ 41:9

በላቸው «እናንተ በዚያ ምድርን **በሁለት ቀኖች** ውስጥ በፈጠረው አምላክ በእርግጥ ትክዳላችሁን? ለእርሱም ባለንጣዎችን ታደርጋላችሁን? ያ (ይህንን የሠራው) የዓለማት ጌታ ነው፡፡ በእርሷም ከበላይዋ የረጉ ጋራዎችን አደረገ፡፡ በእርሷም በረከትን አደረገ፡፡ በውስጧም ምግቦችዋን (ካለፉት ሁለት ቀኖች ጋር) **በአራት ቀናት** ውሰጥ ለጠያቂዎች ትክክል ሲኾኑ ወሰነ፡፡ ከዚያም ወደ ሰማይ እርሷ ጭስ ኾና ሳለች አሰበ፡፡ ለእርሷም ለምድርም «ወዳችሁም ኾነ ወይም ጠልታችሁ ኑ» አላቸው፡፡ «ታዛዦች ኾነን መጣን» አሉ፡፡ **በሁለት ቀኖችም** ውስጥ ሰባት ሰማያት አደረጋቸው፡፡ በሰማይቱም ሁሉ ነገሯን አዘጋጀ፡፡ ቅርቢቱንም ሰማይ በመብራቶች አጌጥን፡፡ (ከሰይጣናት) መጠበቅንም ጠበቅናት፡፡ ይህ የአሸናፊው የዐዋቂው (ጌታ) ውሳኔ ነው፡፡

# ሴቶች ላይ የሚደርስ ኢፍትሀዊነት የሴቶች ከወንዶች ማነስ በክርስትና

- 1ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 2 12

እንዲሁም ደግሞ ሴቶች በሚገባ ልብስ ከእፍረትና ራሳቸውን ከመግዛት ጋር ሰውነታቸውን ይሸልሙ፤ እግዚአብሔርን እንፈራለን ለሚሉት ሴቶች እንደሚገባ፥ መልካም በማድረግ እንጂ በሽሩባና በወርቅ ወይም በዕንቍ ወይም ዋጋው እጅግ በከበረ ልብስ አይሸለሙ። ሴት በነገር ሁሉ እየተገዛች በዝግታ ትማር፤ ሴት ግን በዝግታ ትኑር እንጂ ልታስተምር ወይም በወንድ ላይ ልትሰለጥን አልፈቅድም። አዳም ቀድሞ ተፈጥሮአልና፥ በኋላም ሔዋን ተፈጠረች። የተታለለም አዳም አይደለም፥ ሴቲቱ ግን ተታልላ በመተላለፍ ወደቀች፤ ነገር ግን በእምነትና በፍቅር በቅድስናም ራሳቸውን እየገዙ ቢኖሩ በመውለድ ትድናለች።

# ሴቶች ላይ የሚደርስ ኢፍትሀዊነት የሴቶች ከወንዶች ማነስ በኢስልምና

ሱረቱል አል-ኒሳእ (የሴቶች ምዕራፍ) 4 ፡ 34

ወንዶች በሴቶች ላይ ቋሚዎች (አሳዳሪዎች) ናቸው፡፡ አላህ ከፊላቸውን በከፊሉ ላይ በማብለጡና (ወንዶች) ከገንዘቦቻቸው (ለሴቶች) በመስጠታቸው ነው፡፡ መልካሞቹም ሴቶች (ለባሎቻቸው) ታዛዦች፣ አላህ ባስጠበቀው ነገር ሩቅን ጠባቂዎች ናቸው፡፡ እነዚያንም ማመጻቸውን የምትፈሩትን ገስጹዋቸው፡፡ በመኝታዎችም ተለዩዋቸው፡፡ (ሳካ ሳታደርሱ) ምቱዋቸውም፡፡ ቢታዘዟችሁም (ለመጨቆን) በእነርሱ ላይ መንገድን አትፈልጉ፤ አላህ የበላይ ታላቅ ነውና፡፡

# የቀጠለ...

ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 1፣ ቁ 304

አንዴ የአላህ መልእክተኛ የኢድ አልፈጥር ሰላት ለመስገድ ወደ መስጊድ ሄዱ። ከዛም በሴቶች በኩል በማለፍ እንዲህ አሉ፤ ሴቶች ሆይ ስጦታን ስጡ እኔ እንዳየሁት የገሃነም እሳት አብዛኛው ገቢዎች የሆናችሁት እናንተ ናችሁ። እነርሱም የአላህ መልእክተኛ ለምን ይህ ሆነ? አሏቸው። ሲመልሱም ሁሌ የምትራገሙና የባሎቻችሁን ውለታ ዘንጊዎች ስለሆናችሁ ነው። እኔ እንደ እናንተ በጣም የእውቀትና የሃይማኖት ጉድለት ያለበት ማንንም አላየሁም። በእናንተ በአንዳንዶቹ ጥንቁቅ የሆነው ወንድ ወደ ጥመት ይመራል። ሴቶቹም የአላህ መልእክተኛ በእኛ ያለ የእውቀት ጉድለት ምንድን ነው? ሲሉ ጠየቁ። እርሳቸውም የሁለት ሴቶች ምስክርነት ከአንድ ወንድ ምስክርነት ጋር እኩል አይደለምን? አሉ፤ ሴቶቹም ልክነው አሉ። እርሳቸውም በእውቀት ጎደሎ ማለት ይህ ነው። ደግሞስ ሴት በወር አበባዋ ጊዜ ጾምና ሰላት ማቆሟ እውነት አይደለምን? ሴቶቹም አዎን አሉ። እርሳቸውም በእምነት ጎደሎ ማለት ይህ ነው፤ አሉና መለሱ።134

# ሴቶች ላይ የሚደርስ ኢፍትሀዊነት በኢስልምና

ሱረቱል አል-ኒሳእ (የሴቶች ምዕራፍ) 4 ፡ 34

ወንዶች በሴቶች ላይ ቋሚዎች (አሳዳሪዎች) ናቸው፡፡ አላህ ከፊላቸውን በከፊሉ ላይ በማብለጡና (ወንዶች) ከገንዘቦቻቸው (ለሴቶች) በመስጠታቸው ነው፡፡ መልካሞቹም ሴቶች (ለባሎቻቸው) ታዛዦች፣ አላህ ባስጠበቀው ነገር ሩቅን ጠባቂዎች ናቸው፡፡ እነዚያንም ማመጻቸውን የምትፈሩትን ገስጹዋቸው፡፡ በመኝታዎችም ተለዩዋቸው፡፡ (ሳካ ሳታደርሱ) ምቱዋቸውም፡፡ ቢታዘዟችሁም (ለመጨቆን) በእነርሱ ላይ መንገድን አትፈልጉ፤ አላህ የበላይ ታላቅ ነውና፡፡

# በወር አበባ ምክንያት የሚመጣ መርከስ በክርስትና

ኦሪት ዘሌዋውያን 15 ፡ 19-22

ሴት ፈሳሽ ነገር ቢኖርባት በሥጋዋም ያለው ፈሳሽ ነገር ደም ቢሆን፥ በመርገምዋ ሰባት ቀን ትቀመጣለች፤ የሚነካትም ሁሉ እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ነው። መርገምም ስትሆን የምትተኛበት ነገር ሁሉ ርኩስ ነው፤ 130 ላለመደናገር ማመሳከር (ተሸሽሎ የቀረበ) ገጽ 35 114 የምትቀመጥበትም ነገር ሁሉ ርኩስ ነው። መኝታዋንም የሚነካ ሁሉ ልብሱን ያጥባል፥ በውኃም ይታጠባል፥ እስከ ማታም ድረስ ርኩስ ነው። የምትቀመጥበትንም ነገር ሁሉ የሚነካ ሁሉ ልብሱን ያጥባል፥ በውኃም ይታጠባል፥ እስከ ማታም ርኩስ ነው።

# በወር አበባ ምክንያት የሚመጣ መርከስ በእስልምና

ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ ፩፣ ቁ 305

ከነቢዩ ጋር ሐጅ ለመሄድ ጉዞ ጀመርን፣ ሶሪፍ ላይ ስንደርስ የወር አበባዬ መጣ፡፡ ነቢዩ ወደ እኔ ሲመጡ እያለቀስኩ ነበር፤ ለምን ታለቅሻለሽ? ብለው ጠየቁኝ፡፡ እኔም ምንም እንኳን ሐጅ ለማድረግ ብፈልግም በዚህ ዓመት ማድረግ አልችልም ስል መለስኩላቸው፡፡ ከዛም ይህ አላህ በአደም ሴት ልጆች ላይ የወሰነው ነገር ነው፤ ስለዚህ ያሰብሽውን ሐጅ ፈጽሚ፡፡ ነገር ግን ንጹሕ እስከትሆኚ ድረስ ካእባውን መዞር አትችይም አሉኝ፡፡ አይሻ የተናገረችው

# የቀጠለ

ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 1፣ ቁ 306

ፋጢማ ቢንት አቡ ሁባኢሽ ለአላህ መልእክተኛ እንዲህ አለች፤ የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ ከደም መፍሰስ ንጹህ አልሆንኩም፡፡ ታዲያ ሰላት መስገድ ላቁምን? የአላህ መልእክተኛም ሲመልሱ፣ አታቁሚ ይህ ደም መፍሰስ፣ ከደም ስር እንጂ የወር አበባ አይደለም፡፡ ስለዚህ ትክክለኛው 132 SAHIH AL-BUKHARI VOL 1, PAGE 211 116 የወር አበባሽ መፍሰስ ሲጀምር ሰላት አቁሚ፡፡ የወር አበባሽ በቆመ ጊዜ ደግሞ በውሃ ታጠቢ፣ ሰላት ማድረግሽንም ጀምሪ፡፡133

# የመጽሀፍ ቅዱስ በተለያዩ ቅጂዎች ውስጥ መበረዝ

ዮሀ 5

1ከዚህ በኋላ የአይሁድ በዓል ነበረ፤ ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ። 2በኢየሩሳሌም፣ በበጎች በር አጠገብ፣ አምስት ባለ መጠለያ መመላለሻዎች
የነበሯት፣ በአራማይክ ቋንቋ ቤተ ሳይዳ የተባለች አንዲት መጠመቂያ አለች። 3በእነዚህም መመላለሻዎች ውስጥ ብዙ አካለ ስንኩላን፣ ዐይነ ስውሮች፣
ዐንካሶችና ሽባዎች ይተኙ ነበር። [የውሃውንም መንቀሳቀስ እየተጠባበቁ፣ 4ዐልፎ ዐልፎ የጌታ መልአክ ወርዶ ውሃውን በሚያናውጥበት ጊዜ፣ ቀድሞ
ወደ መጠመቂያዩቱ የገባ ካደረበት ማንኛውም በሽታ ይፈወስ ነበር።]

ከዚህ በኋላ የአይሁድ በዓል ነበረ፥ ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ። 2 በኢየሩሳሌምም በበጎች በር አጠገብ በዕብራይስጥ ቤተ ሳይዳ የምትባል
አንዲት መጠመቂያ ነበረች፤ አምስትም መመላለሻ ነበረባት። 3 በእነዚህ ውስጥ የውኃውን መንቀሳቀስ እየጠበቁ በሽተኞችና ዕውሮች አንካሶችም
ሰውነታቸውም የሰለለ ብዙ ሕዝብ ይተኙ ነበር። 4 አንዳንድ ጊዜ የጌታ መልአክ ወደ መጠመቂያይቱ ወርዶ ውኃውን ያናውጥ ነበርና፤ እንግዲህ
ከውኃው መናወጥ በኋላ በመጀመሪያ የገባ ከማናቸው ካለበት ደዌ ጤናማ ይሆን ነበር። 5 በዚያም ከሠላሳ ስምንት ዓመት ጀምሮ የታመመ አንድ ሰው
ነበረ፤ 6 ኢየሱስ ይህን ሰው ተኝቶ ባየ ጊዜ፥ እስከ አሁን ብዙ ዘመን እንዲሁ እንደ ነበረ አውቆ። ልትድን ትወዳለህን? አለው።

# በተለያዩ የቁራን ቅጆች ውስጥ ያሉ የተለያዩ ይዘቶች

በዚህ በእኛ ዘመን ሰባት መሠረታዊ ልዩነቶች ያሏቸው 38 የአረብኛ ቁርአን አሉ

ያሉባቸው ልዩነቶች ፡-

- የአነባበብ ልዩነት
- የአናባቢ ስርአተ ነጥቦች ፣ የፊደላትና የቃላት ልዩነቶች
- የቃላት ለውጥና የአንቀጾች ቁጥር አሰጣጥ ልዩነት
- የቃላት ቅደም ተከተል ልዩነት
- የቃላት ወይም የፊደላት ጭማሬና ቅነሳ
- የቃላት አወቃቀር ልዩነት ለምሳሌ ብዙ ቁጥር ወደ ነጠላ ወይም ሁለት ወይም የተለየ ለውጦች መቀየር፣ አነስታይ ጾታ የሆነ ወደ ተባዕታይ ጾታ መቀየር ይታይባቸዋል
- የቃላት አረባብ ወይንም አሰባበር ነጥቦች ልዩነት ናቸው

- ስለዚህ በዚህ ምክንያት አሁንም ቁርአን በራሱ የመለኮታዊ መጽሐፍት መለኪያ ከመለኮታዊ መጽሐፍት ጎራ ውድቅ ሆኗል
- HTTPS://WWW.ANSWERING-ISLAM.ORG/GREEN/SEVEN.HTM
- HTTPS://WWW.YOUTUBE.COM/WATCH?V=XV2E70G66QI